በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቀን ምክቶ 11 2012
Date
ቁጥር 4-0/0353/12
Ref.No.

በአባሪው ለተዘረዘሩት የጉ/ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
በያሉበት

የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ በቁጥር ስጉኤ/02/350/2012 ቀን 06/06/2012 በተጻፈ ደብዳቤ ኤጀንሲው ወደ ሀገራችን ለሚመጡ ስደተኞች በእርዳታ የሚያገኛቸው ዕቃዎች፣ ተሽከርካሪዎችና ግብዓቶች በኤጀንሲው ስም ወይም በባለድርሻ አካላት በኩል ወደ ሀገር ውስጥ ሲያስገባ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 47- 49 መሠረት ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲገቡ የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ.30/7/2 በቀን 23/11/2011 በጻፈው መሠረት አገልግሎት እንዲሰጥ ጠይቋል፡፡

የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ.30/7/2 በቀን 23/11/2011 ለኤጀንሲው በጻፈው ደብዳቤ ከዚህ ቀደም የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት በተለያዩ አደጋዎች ምክንያት ተፈናቅለው በስደት ወደ ሀገራችን ለሚመጡ ሰዎች አገልግሎት እንዲውል ወደ ሀገር የሚያስገባቸው የዕርዳታ ዕቃዎች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ከአንቀጽ 47 - 49 መሠረት ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲገቡ መመሪያ መተላለፉን በማስታወስ ኤጀንሲው የአደጋ ተጎጂዎች መርጃ እንዲውሉ በእርዳታ የሚያገኛቸውን ዕቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነጻ የማድረጉ አሠራር በህጉ አግባብ እንዲቀጥል አሳውቋል፡፡

በመሆኑም የገንዘብ ሚኒስቴር በሠጠው አቅጣጫ መሠረት የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ የአደጋ ተጎጂዎች መርጃ እንዲውሉ በእርዳታ የሚያገኛቸውን ዕቃዎች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ከአንቀጽ 47 - 49 መሠረት ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲስተናገዱ እየገለጽን፤ የኤጀንሲውን 01 ገጽ እና የሚኒስቴር መ/ቤቱን 02 ገጽ በድምሩ 03 ገጽ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ወንድወሰን ደገፋ ካሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን የጽ/ቤት ኃላፊ

ግልባጭ
- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለዕቃ አወጣጥ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስና ኮንትሮባንድ መከላከል ዳይሬክቶሬት

ጉምሩክ ኮሚሽን

- ለታክስ እና ጉምሩክ መረጃ፤ ማብራሪያ እና ምክር አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

ገቢዎች ሚኒስቴር

ለዘመናዊና ፍትሀዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

☎ +251 116 62 98 00
📠 +251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  አዲስ አበባ
- ለሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ሞጆ
- ለአዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  አዳማ
- ለድሬዳዋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ድሬዳዋ
- ለጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ጅግጅጋ
- ለሀዋሳ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ሀዋሳ
- ለጅማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ጅማ
- ለሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ሞያሌ
- ለአዋሽ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  አዋሽ
- ለጋላፊ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ጋላፊ
- ለኮምቦልቻ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ኮምቦልቻ
- ለመቀሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  መቀሌ
- ለባህር ዳር ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ባህርዳር

1305
6/6/12


በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Agency for Refugee and Returnee Affairs


ቁጥር ስገጉ/02/350/2012
Ref. No.
ቀን 06/06/2012
Date

ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የጉምሩክ ኮሚሽን

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>ቀረጥና ታክስን ይመለከታል</u>

መ/ቤታችን የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ በተለያዩ አደጋዎች ምክንያት ተፈናቅለው በስደት ወደ አገራችን ለሚመጡ ስደተኞች በእርዳታ የሚያገኛቸው ለመሰረታዊና ለማህበራዊ አገልግሎቶች የሚውሉ እቃዎች እንዲሁም ለአገልግሎቱ ማስፈፀሚያ የሚውሉ ተሽከርካሪዎችና ግብዓቶች በኤጀንሲው ስም ወይም በባለድርሻ አካላት በኩል ወደ ሃገር ውስጥ ሲያስገባ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 47-49 መሰረት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተላለፈው መመሪያ እንደሚቀጥል የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ማኢ30/7/2 በቀን 23/11/2011 በተፃፈ ደብዳቤ ተገልፆልናል፡፡

ስለሆነም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፃፈውን ደብዳቤ ኮፒ 2 ገፅ አባሪ አድርገን መላካችንን እየገለፅን፤ ጉዳዩን ሁሉም የቅርንጫፍ መ/ቤቶቻችሁ አውቀውት በዚህ አግባብ እንዲያስተናግዱን እንዲደረግ የተለመደ ትብብራችሁን እንጠይቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ከበደ ጫኔ
ዋና ዳይሬክተር


ስልክ Tel. +251 11 155 11 11 ፋክስ Fax. +251 11 155 20 08 ኢሜል E-mail info@arra.et ፖ.ሣ.ቁ P.O. Box 84 አዲስ አበባ Addis Ababa
Website: www.arra.et

ስ/ጉ ኤ.
ተቀብለናል
ቀን 01/12/11
ፊርማ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No. ገሚ23017/2
ቀን
Date 23/11/2011

ለየስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ

<u>አዲስ አበባ</u>

የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ በቅርቡ በወጣው የፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር የሚወስነው አዋጅ ቁጥር 1097/2018 መሰረት ለሰላም ሚኒስቴር ተጠሪ መ/ቤት መሆኑን ገልፃችሁ አገራችን ስደተኞችን በተመለከተ በዓለም አቀፍና በአህጉር ደረጃ የወጡና የተቀበለቻቸውን ኮንቬንሽኖች ፣ ፕሮቶኮሎች እና ሌሎች ስምምነቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለውን የህዝብለ ህዝብግንኙነት ዘለቄታዊና ስታራቴጂክ ተጠቃሚነቶችን በሚያረጋግጥ መልኩ የሰመረ መሆንን ታሳቢ ለማድረግ በአሁኑ ሠዓት ከ26 ሀገራት የተሰደዱ ቁጥራቸው አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ስደቶችን ከመቀበል ጀምሮ ወደ አገራቸው ለመመለስ የሚያስችሉ ሁኔታዎች እስኪመቻቹ ድረስ ማህበራዊ እና መሰረታዊ አገልግሎቶች እንዲያገኙ እንዲሁም በሌሎች ሀገሮች በUNHCR እውቅና ተሰጥቷቸው ተመዝግበው የቆዩና ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ፍቃደኛ የሆኑ ኢትዮጵያውያንን ወደ ነበሩበት ማህበረሰብ ተቀላቅለው እንዲኖሩ የማድረግ ስራን የሚሰራ መሆኑን ገልፃችሁ ለእነዚህ ስራዎች የሚውሉ እና ስራውን ለማከናወን የሚያስችሉ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች ግብዓቶች ከአለም አቀፍ ማህበረሰብ እና ከለጋሽ ሀገራት ድርጅቶች በእርዳታ የሚቀርቡ በመሆኑ ከዚህ በፊት የነበረው የቀረጥና ታክስ ነፃ የማድረጉ አሰራር እንዲቀጥል ለገቢዎች ሚኒስቴር እና ለጉምሩክ ኮሚሽን እንዲገለፅልን በማለት በቀን 26/10/2011 ዓ.ም በቁጥር ስጉኤ/02/301/2011 በተፃፈ ደብዳቤ መጠየቃችሁ ይታወሳል፡፡

ከዚህ ቀደም የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ጥያቄ አቅርቦ መ/ቤታችን ሕዳር 04 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ታ/ክ/ቀ/5/94 እንዲሁም ግንቦት 23 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ታ/ክ/ቀ/5/287 በተፃፈ ደብዳቤ የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት በተለያዩ አደጋዎች ምክንያት ተፈናቅለው በስደት ወደ አገራችን ለሚመጡ ሰዎች አገልግሎት እንዲውሉ ወደ አገር የሚያስገባቸው የዕርዳታ ዕቃዎች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ከአንቀፅ 47-49 መሠረት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መመሪያ መተላለፉ የሚታወስ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የጉምሩክ ኮሚሽን
ዶ/ መዝገብና ዶክመንቴሽን
ቁጥር፡ 2
No.2
Ethiopian Customs Commission
Records Documentation

ስልክ
Tel 251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲጽፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ
Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia

ስለሆነም አጀንሲው የአደጋ ተጎጂዎች መርጃ እንዲውሉ በእርዳታ የምታገኞዋቸውን  እቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ የማድረጉ አሰራር በህጉ አግባብ እንዲቀጥል እና ለክትትልና ለግምገማ እንዲያመች ዘንድ በቀጣይ በእርዳታ የሚገቡትን የዕቃ ዝርዝሮች ከነመጠናቸው እንድትገልፁልን እንጠይቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

መሳይ ወልዱ
ታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር